ስለ አውሮጳ መንገድ

# የምክር

ቃል ።

በልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ
መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ።

ስለ አውሮጳ መንገድ

# የምክር

ቃል ።

በልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ
መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ።

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ።

## ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል።

ለትምህርትም ቢሆን ፤ ለንግድም ቢሆን ፤ ወይም ከመንግሥት ተልከም ቢሆን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሚሔድ ሰው ሁሉ ይህን የምክር ቃል ማንበብ ይገባዋል።

## ስለ ይለፍ ወረቀት ፓስፖርት።

፩ኛ ወደ ውጭ አገር ለመሔድ የሚፈልግ የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ለመንገዱ መነሣት ፲፭ ቀን ሲቀረው የይለፍ ወረቀቱን ነገር መጨረስ ያስፈልገዋል። ይህንም የይለፍ ወረቀት መቀበል የሚያስፈልገው መጀመሪያ ከኢትዮጵያ መንግሥት ነው።

፪ኛ የይለፍ ወረቀቱን ከኢትዮጵያ መንግሥት ከተቀበለ በኋላ የሚሔድበትን አገር አስታውቆ ወደ ሌጋሲዎን ሔዶ የቆንስሉን ፊርማ በይለፍ ወረቀቱ ላይ ማስፈረም ነው። በየመንግሥቱም የሚሔድ የሆነ እንደሆነ በአዲስ አበባ ከሚኖሩት ቆንስሎች ሁሉ ማስፈረም ያስፈልጋል።

## ስለ መርከብ መገኘት።

፫ኛ መርከብ ጅቡቲ የሚገኝበትን ጊዜ ከ፲፭ ቀን በፊት ማወቅ ያስፈልጋል። ይህንኑም ለማወቅ በጅቡቲ ወዳጅና ዘመድ ያለው ሰው በጽሕፈት ወይም በቴሌግራም መጠየቅ ያስፈልጋል። በጅቡቲ ወዳጅና ዘመድ የሌለው ግን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ቆንስል ቤት ለመጠየቅ ይችላል።

፬ኛ መርከቡ ጅቡቲ የሚገኝበት ጊዜው ከታወቀ በኋላ ስለ ቦታው እንደአቅሙ በመጀመሪያው ፤ ወይም በሁለተኛው ወይም በሶስተኛው ማዕርግ ቦታ መገኘቱን ከኩምፓኒያው ጠይቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ቦታው መገኘቱ እርግጡ ከታወቀ በኋላ መር

ከቡ ከጅቡቲ ከሚነሣበት ጊዜ ከሁለት ቀን በፊት ጅቡቲ መድረስ ያስፈልጋል ።

## በምድር፡ባቡር ስለመሣፈር ።

፩ኛ በመንግሥት ፈቃድ በእኩሌታ ዋጋ በባቡር የሚሳፈር ሰው ካንድ ቀን በፊት የፈቃድ ወረቀቱን መቀበል ያስፈልገዋል ።

፪ኛ ባቡሩ ለመነሣት አንድ ሰዓት ሲቀረው በባቡር፡መቆሚያ ደርሶ የባቡሩን መግቢያ ወረቀት ለመቀበል ገንዘቡን መክፈል ነው ። ብዙ ዕቃ ያለው ሰው ግን ከ፪ ሰዓት አስቀድሞ በባቡር መቆሚያ ደርሶ ዕቃውን ማሳፈር ያስፈልገዋል ። ዕቃውንም ሲያሳፍር ከኩምፓኒያው የደረሰኝ መቀበል ያስፈልገዋል ። ነገር ግን ይህ የሚቀበለው የደረሰኝ የጠፋ እንደሆነ ኩምፓኒያው አላፊነት የለበትምና ተጠንቅቆ መጠበቅ ነው ።

፫ኛ በባቡር የሚሳፈር ሰው የመቀመጫውን ስፍራ ሌሎች ሰዎች ሳይዙበት በቶሎ ገብቶ ባርኔጣውን ወይም የብርድ ልብሱን ፤ ወይም መጽሐፉን በመቀመጫው ላይ ማኖር ያስፈልገዋል ይህን ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ግን ወደውጭ በወጣ ጊዜ ሌላ ሰው ገብቶ ስፍራውን ሊይዝበት ይችላል ።

፬ኛ በባቡር ውስጥ በሣጥን ያልገባ ትንንሽ ዕቃ የያዘ ሰው በጣም ተጠንቅቆ መጠበቅ ያስፈልገዋል ። ሻንጣውንም ደህና አድርጎ መቆለፍ ነው ።

፭ኛ ባቡር በየጣቢያው በሚቆምበት ጊዜ የሚቆመው ስንት ደቂቃ መሆኑን ሳያውቁ ወደ ምድር መውረድ አይገባም ። የሚቆምበት ጊዜ ስንት ደቂቃ እንደሆነ ሳያውቁ ወደ ምድር የወረዱ እንደሆነ ባቡሩ በድንገት በተነሣ ጊዜ ሮጦ ለመግባት ብዙ ችግር ይሆናል ።

፮ኛ በየጣቢያው ባቡሩ በቆመ ጊዜ በባቡሩ ውስጥ ባለው ሠገራ ቤት ገብቶ ሽንት መሽን ሌላም ጉዳይ ማድረግ አይገባም ። ይህን የመሰለውን ጉዳይ ሁሉ መፈጸም ባቡሩ በሚሄድበት ጊዜ ነው ።

፲፩ኛ ባቡሩ በሚሔድበት ጊዜ ሁሉ በመስኮት አንገትን ወይም እጅን ብቅ ማድረግ ክልክል ነው ፡፡ ብቅ ያደረገ እንደሆነ ግን ከባቡሩ ፍጥነት የተነሣ ከእንጨት ጋራ ወይም ከገደል ጋራ አጣብቆ ይቆርጠዋል ፡፡

፲፪ኛ ከባቡር ለመውረድ ጊዜው በደረሰ ጊዜ ዕቃን ሁሉ በጥንቃቄ ማውረድ ያስፈልጋል ፡፡ ዕቃውም ከወረደ በኋላ የሚሸከሙት ኩሌዎች ተሸካሚዎች ኑሜሮአቸው በክንዳቸው ወይም በቆባቸው ይጻፋልና በጥንቃቄ አይቶ ኑሜሮውን በቶሎ መጻፍ ነው ፡፡

፲፫ኛ ዕቃው ሁሉ ከባቡር ከወረደ በኋላ የጉምሩኩን ጣጣ ጨርሶ ወደ ሆቴል ወይም ወደ ዘመድ ቤት ዕቃን አሸክሞ መሔድ ነው ፡፡

፲፬ኛ ጅቡቲ በደረሱ በማግሥቱ ወደ ዘበኛ አለቃ ጽሕፈት ቤት ሔዶ የይለፍ ወረቀቱን አሣይቶ በላዩ ማስፈረም ነው ፡፡ ከዚህም በኋላ ወደ መርከቡ ኩምፓኒያ ሔዶ ገንዘቡን ከፍሎ የመርከቡን መግቢያ ወረቀት (ቢዬ) መቀበል ያስፈልጋል ፡፡

## ወደ መርከብ ስለ መግባት ፡፡

፲፭ኛ መርከቡ ጅቡቲ ከገባ በኋላ ብዙ ዕቃ ያለው ሰው በፍጥነት ጀልባ ተከራይቶ አስቀድሞ ዕቃውን አግብቶ የደረሰኝ መቀበል ያስፈልገዋል ፡፡ የልብስ ሻንጣ ብቻ የያዘ ሰው ግን እርሱ በሚገባበት ጊዜ ይዞ ለመግባት ይችላል ፡፡

፲፮ኛ መርከቡ ለመጓዝ አንድ ሰዓት ሲቀረው ወደ መርከብ መግባትና ስፍራን ተቀብሎ መቆየት ያስፈልጋል ፡፡

፲፯ኛ ወደ መርከብ በመግባት ጊዜ በመጀመሪያ የመርከቡን መግቢያ ወረቀትና የይለፍ ወረቀቱን ለመርከቡ ሹሞች ማሳየት ያስፈልጋል ፡፡

፲፰ኛ በመርከብ ውስጥ የመኝታ ስፍራ ከመቀበል በኋላ በፍጥነት የሠገራ ቤቱንና የመታጠቢያ ቤቱን ፣ ቀጥሎም የምግቡ

ን ቤትና የጽሕፈት ቤቱን ፤ የመጻሕፍት ማንበቢያ ቤቱን ማየትና ማወቅ ያስፈልጋል ።

፲፱ኛ በመርከብ ውስጥ ለቁርስ ፥ ለምሳ ፥ ለሻይ ፥ ለራት ፤ የተወሰነውን ሰዓት ማወቅና በጊዜው ከሥፍራው መገኘት ይገባል ። ሰዓቱ ካለፈ በኋላ ግን ምንም ለማግኘት አይቻልም ።

፳ኛ በመርከብ ውስጥ አልማዝና ወርቅ ሌላም ክቡር ዕቃ ያለው ሰው ሁሉ ተጠንቅቆ መጠበቅ ይገባዋል ። ለመጠበቅ የማይችል የሆነ እንደ ሆነ ግን ለመርከቡ ሹም አስረክቦ የደረሰኝ መቀበል ነው ። ክቡር ዕቃውን ተጠንቅቆ ሳይጠብቅ ወይም ለመርከቡ ሹም ሳያስረክብ ቀርቶ የጠፋበት እንደሆነ የመርከቡ ኩምፓኒያ አላፊነት የለበትም የሚል ደምብ አላቸውና በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

፳፩ኛ በመርከብ ውስጥ ሰው ሁሉ በየስፍራው አርፎ መቀመጥ ነው እንጂ የሶስተኛው ማዕርግ ወደሁለተኛው ፤ የሁለተኛው ማዕርግ ወደመጀመሪያው ፤ እንዳይተላለፍ ክልክል ነው ። ነገር ግን ለብርቱ ጉዳይና ሰው ለመገናኘት ፤ አሽከር ከጌታው ትእዛዝ ለመቀበል ቢፈልግ ላንድ አፍታ መተላለፍ አይከለከልም ።

፳፪ኛ ወደመርከብ የሚገባ ሰው ሁሉ አንዳንድ ምቹ ወምበር ይዞ መግባት ያስፈልጋል ። ወይም የመርከቡ ኩምፓኒያ ወምበር ያከራያልና መከራየት ነው ። ለጊዜው ባለቤቱ ባይኖር እንኳ በሌላ ሰው ወምበር ላይ መቀመጥ ክልክል ነው ።

፳፫ኛ በመርከብ ውስጥ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ማዕርግ የሚገባ ሰው በእራት ጊዜ ጥሩ ጥሩ ልብስ መልበስ ያስፈልገዋል

፳፬ኛ በመርከብ ውስጥ ባዳራሹ (ሳሎን) ወይም በመናፈሻው ስፍራ ፥ በትልልቆች ሰዎችና በወይዛዝር ፊት ነጠላ ጫማ አድርጎና የሌሊት ልብስ ለብሶ መቀየትና መሄድ ትልቅ ነውር ነው

፳፭ኛ በመርከብ ውስጥ የኤሌክትሪኩን መብራት ፀሐይ ከጠለቀች ጀምሮ ፀሐይ እስክትወጣ ባስፈለገ ጊዜ ማብራት አይከለከልም ። ፀሐይ ከወጣች በኋላ ግን የመብራቱን መኪና ማቆም ይገባል ።

፳፮ኛ በመርከቡ ውስጥ ሙቀት በጸና ጊዜ ነፋስ የሚያመጣውን የኤሌክትሪክ መኪና በስፈለገ ጊዜ መዘወር ነው ። ባላስፈለገና ወደውጭ በመውጣት ጊዜ ግን መኪናውን አቁሞ መውጣት ይገባል ።

፳፯ኛ ወደሠገራ ቤት በመግባት ጊዜ መዝጊያውን ከወደውስጥ አጠንክሮ መዝጋት ያስፈልጋል ። ጉዳይንም ጨርሶ በመውጣት ጊዜ ባጠገብ በተሰቀለው ውኃ እድፉ እንዲወርድና ንጹሕ እንዲሆን ማድረግ ነው ። እድፉን በውኃ ንጹሕ ሳያደርጉ ከሠገራ ቤት መውጣት ትልቅ ነውር ነው ። በኋላም መዝጊያውን ከፍቱን ትቶ መውጣት ነው እንጂ ዘግቶ መውጣት አይገባም

፳፰ኛ በመርከቡ ውስጥ በየመኝታው ቤት ደወል አለና የቸገረ ነገር የተገኘ እንደሆነ በጣት ጫን አድርጎ መደወል ነው የመርከቡ አገልጋይ ደወሉን ሰምቶ ያልመጣ እንደሆነ ሶስት ደቂቃ ያሀል ቆይቶ መደወል ነው ።

፳፱ኛ በመርከብ ውስጥ ማታ ማታ ጫማን አውልቆ በመዝጊያው በስተውጭ ማስቀመጥ ነው ። በማለዳ ጫማ ጠራጊ መጥቶ ጠርጎ ወልውሎ መልሶ በዚያው ስፍራ አስቀምጦት ይገኛል

፴ኛ በመርከብ ውስጥ ጧት ከ፫ ሰዓት በኋላ ከመኝታ ቤት ወጥቶ በመናፈሻው ስፍራ ወይም በመጽሐፍ ማንበቢያው ስፍራ መቀመጥ ነው ። በዚያ ጊዜ ቤት ጠራጊ ወደ መኝታ ቤት ገብቶ ስፍራውን ንጹሕ አድርጎ አልጋውን አንጥፎ ይወጣል ቤቱ ከተጠረገ በኋላ ቢያስፈልግ ተመልሶ ለመግባት ይሆናል ።

፴፩ኛ በመርከብ ውስጥ በየእለቱ ወይም በሁለት በሁለት ቀን ልብስ መለወጥ ያስፈልጋል ።

፴፪ኛ በመርከብ ውስጥ በየለቱ ወይም በሁለት በሁለት ቀን ሙሉ አካልን መታጠብ ያስፈልጋል ። ለዚሁ የሚያስፈልገውን ሳሙና ፤ ፎጣ ፤ ሰፍነግ መያዝ ነው ። ወደ መታጠቢያ ቤት በመግባት ጊዜ ከወደ ውስጥ መዝጊያውን አጠንክሮ መዝጋት ነው ። ከ፲ ደቂቃ የበለጠ በመታጠቢያ ቤት መቆየት አይገባም ።

፴፫ኛ በመርከብ ውስጥ የመርከቡ ሹም ሳይፈቅድ ምግብ ወደሚሰናዳበት ፤ ወጥ ወደሚቀቀልበት ስፍራ መግባት አይገባም

ደግሞ አለፈቃድ መርከቡን የሚያስኬደውን መኪና ለማየ ት መግባት ክልክል ነው።

፹፩ኛ መርከቡን የሚያስኬደውን መኪና ለማየት ፈቃድ ተቀ ብሎ በመግባት ጊዜ ብዙ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።መኪናው እ ርስ በርሱ የተቀራረበና የተያያዘ ስለ ሆነ ልብስ ጠልፎ የያ ዘ እንደሆነ የሞት አደጋ ያመጣል ስለዚህ ወደ መኪናው አለመቅረብ ያስፈልጋል።

፹፪ኛ ወንዶች ወደ ሴቶች ሠገራ ቤትና መታጠቢያ ቤት እንዳ ይገቡ ክልክል ነውና ሥፍራውን ተጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

፹፫ኛ ከመርከብ በመውረድ ጊዜ ለመርከብ አገልጋዮች እን ደ ተቻለ ጥቂት ጥቂት ገንዘብ መስጠት ያስፈልጋል።

፹፬ኛ ከመርከብ በመውጣት ጊዜ በፍጥነት ዕቃን ማውጣት ይገባል።የጠፋ ዕቃም ቢኖር የደረሰኝ ወረቀት ካልጠፋ የመ ርከቡ ኩምፓንያ አላፊ ይሆናልና የደረሰኙን ለመርከቡ ሹም ማሳየት ነው።

## በመርከብም፤በባቡርም፤በሆቴልም በማና ቸውም ስፍራ ቢሆን ለማድረግ የማይገባ።

፹፰ኛ በማናቸውም ሥፍራ ቢሆን ልብስን አንፍጫ ላይ ማድረ ግ ወይም ራስን መከናነብ አይገባም።

፹፱ኛ ጧት ጧት ራስን ፊትን ሳይታጠቡ ወደ ውጭ መውጣት አይገባም ደግሞ በጥርስ ቡርሽና በሳሙና ጥርስን አፍን ማ ታጠብ ነው።ደግሞ በጥፍር ውስጥ እድፍ እንዳይታይ በየጊ ዜው ማውጣት ያስፈልጋል

፺ በትልልቅ ሰዎች ፊት ይልቁንም በወይዛዝር ፊት ጥርስን መፋቅ ከጥፍር ውስጥ እድፍ ማውጣት አይገባም።

፺፩ ከትልልቅ ሰዎች ጋራ ይልቁንም ከወይዛዝር ጋራ ሲነጋገ ሩ እግርን አጣምሮ መቀመጥ መጨጊያ ተንተርሶ በጉድን መ ጋደም አይገባም።

፺፩ ትልልቅ ሰዎች ይልቁንም ወይዛዝሮች ለመጠየቅ በመጡ ጊዜ ከወምበር ተነስቶ ቆሞ አክብሮ መቀበል ይገባል ። ተቀምጦ እንግዳ መቀበል ግን ትልቅ ነውር ነው ። ትልቅ እንግዳ በመጣ ጊዜ አክብሮ ተቀብሎ በብሩህ ገጽ በደስታ ማነጋገር ነው እንጂ ፊትን አጥቁሮ ተከፍቶ ማነጋገር አይገባም ። ደግሞ ትልቅ እንግዳ ተቀምጦ ሳለ እርሱን ማነጋገር ትቶ ጋዜጣ ማንበብ ጽሕፈት መጻፍ አይገባም ።

፺፪ ትልቅ እንግዳ በመጣ ጊዜ በንግግሩ መካከል ሰዓት አውጥቶ ማየት ለባለቤቱ አይገባውም ። እንግዳ ተቀምጦ ሲነጋገር ሰዓት አውጥቶ ማየት ሒድልኝ ከማለት ይቆጠራል ። ነገር ግን ወደ ሰው ቤት ሔዶ ጉዳዩን የሚነጋገር ሰው በንግግሩ መካከል ሰዓት አውጥቶ ቢያይ እርሱ ለመሔድ መቸኰሉን ያስረዳልና ነውር የለበትም ።

፺፫ በመብልና ባካሄድ በመቀመጥም ጊዜ ወይዛዝርን መቅደም አይገባም በስፍራውም ያለው ወምበር ለሁሉ የማይበቃ የሆነ እንደሆነ ወምበሩን ለወይዛዝር ለቆ መቆም ይገባል ።

፺፬ ከትልልቆች ሰዎች ጋራ በመነጋገር ጊዜ ፊት ለፊት ሆኖ ዓይን ላይን እየተያዩ መነጋገር ነው እንጂ ፊትን አዙሮ ወይም በዓይን ሌላ ነገር እያዩ መነጋገር አይገባም ።

፺፭ በቤተ መንግሥትም ቢሆን በፋብሪካም ቢሆን የሚታይ ነገር ለማየት በመግባት ጊዜ ልብን አንቅቶ እንደዋዛ ዓይንን ጣል አድርጎ ማየት ነው እንጂ ከባላገር እንደመጣ ሰው ዓይንን እያቅበዘበዘ ማየት አይገባም ።

፺፮ በሰውም ፊት ቢሆን ለብቻም ቢሆን አክ ብሎ አክታ ወደምድር መትፋት አይገባምና በቀስታ አክ ብሎ በመሐርም መቀበል ነው ። በመናፈጥም ጊዜ አፍንጫን በመሐርም አጥብቆ ይዞ በቀስታ መናፈጥ ነው እንጂ ድምጡን አሰምቶ በኃይል መናፈጥና ወደምድር መጣል አይገባም ።

፺፯ ቡን ወይም ሾርባ በመጠጣት ጊዜ ሙቀቱ ሲበርድ በቀስታ ሳብ አድርጎ መጠጣት ነው እንጂ ትንፋሽን አሰምቶ ፉት ማድረግ አይገባም ።

## ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል።

፺፱ በምግብ ጊዜ ወጡን በትንሹ መውሰድ ነው እንጂ በብዙ መውሰድ አይገባም ፡፡ ቢያስፈልግ ግን እንደገና መውሰድ አይከለከልም ።

፻ በምግብ ጊዜ አፍን ገጥሞ በቀስታ ማላመጥ ነው እንጂ አፍን ከፍቶ መመገብና አፍን እያጮሁ ማላመጥ አይገባም ።

፻፩ በምግብ ጊዜ ወይም በሌላ ጊዜ ብዙ መጠጥ መጠጣት ነውር ነው ። የወይን ጠጅም በመጠጣት ጊዜ ውኃ እየደባለቁ መጠጣት ነው እንጂ ብቻውን መጠጣት ሰውነት ይጎዳል።አረቄ መጠጣት ለትልቅ ሰው በጭራሽ ቢቀርበት መልካም ነው።ለመተው የማይችል ሰው ግን አንድ መለኪያ ብቻ ይጠጣ እንጂ ከዚህ የበለጠ ቢጠጣ ነውር ይሆንበታል ።

፻፪ በቤተ መንግሥትና በሌላም በትልልቅ ስፍራ በቤተ ክርስቲያንም ፤ በትልልቅ ሰዎችም ፊት ቀስ ብሎ በእርጋታ መሄድ ነው እንጂ የጫማ ድምጥ እስቲሰማ እየረገጡና እየተገላመጡ መሄድ አይገባም ።

፻፫ ከትልቅ ሰው ጋራ በመነጋገር ጊዜ በለዘብታና በቀስታ ቃል መነጋገር ነው እንጂ እየጮሁ መነጋገር አይገባም ።በመሳቅም ጊዜ ጥርስን ፍግግ ፍግግ እያደረጉ መሳቅ ነው እንጂ በውጭ እስቲሰማ ድረስ እየተንከተከቱ መሣቅ አይገባም።

፻፬ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በመሸታ ቤትና በጋለሞታ ሰፈር ተቀምጦ መታየት ትልቅ ነውር ነው ።

፻፭ በከሐዲም ባቀማመጥም ጊዜ ባለማዕርጉን ማክበር ነው እንጂ ትንሽ ማዕርግ ያለው ትልቅ ማዕርግ ያለውን መቅደም አይገባም ።

፻፮ በንግግር ጊዜ የተጠየቀው ሰው ሳይናገር ያልተጠየቀው ሰው ለመናገር አይገባውም ። በነገሩም መከከል ማሰናከል አይገባም ።

አዲስ ፡ አበባ ፡
Addis Ababa
Library